የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 14
ADDIS ABABA 22nd January, 2007

**ማ ው ጫ**

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፬/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር የማሻሻያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ …. ገጽ ፫ሺ፭፻፴፪

**CONTENTS**

**Proclamation No. 514/2007**

The Proclamation to Amend the Daradawa Administration Charter (Amendment) Proclamation…….. Page 3532

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፬/፲፱፻፺፱

## የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር ማሻሻያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በድሬዳዋ አስተዳደር በህዝብ የተመረጠ ምክር ቤት እስኪመሰረት ድረስ በጊዜያዊ አስተዳደር እንዲመራ በህግ የተደነገገ በመሆኑ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፫/፲፱፻፺፰ ዓ.ም መሠረትም የጊዜያዊ አስተዳደሩ የሥራ ጊዜ የሚጠናቀቀው ታህሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በመሆኑ፤

የአስተዳደሩን የምክር ቤት ምርጫ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች ያልተጠናቀቁ በመሆናቸው እና ይህንንም ምርጫ የጊዜያዊ አስተዳደሩ የሥራ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ማከናወን ባለመቻሉ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር የምክር ቤት ምርጫ እስከ ሚከናወን ድረስ የአስተዳደር ክፍተት እንዳይፈጠር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 514/2007.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE DIREDAWA ADMINISTRATION CHARTER (AMENDMENT) PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has been proclaimed that the Diredawa Administration should be led by provisional Administration until the establishment of Council elected by the people;

**WHEREAS,** in accordance with the Diredawa Administration charter (Amendment) proclamation No 483/2006, the term of the provisional Administration expires on January 4, 2007;

**WHEREAS,** the preconditions to Undertake the Administration Council election has not been fulfilled and it has become impossible to conduct the election prior to the expiry of the provisional Administration's term;

**WHEREAS,** it has become necessary to avoid Administration vacuum until the Diredawa Administration Council election takes place;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር የማሻሻያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፬/፲፱፻፺፱ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. ማሻሻያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፫/፲፱፻፺፰ ዓ.ም አንቀፅ ሁለት እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

> "፪ የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የስራ ጊዜ እስከ ሰኔ ፴/፲፱፻፺፱ ዓ.ም ድረስ ተራዝሟል"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጀምር የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Proclamation to Amend the Diredawa Administration Charter (Amendment) Proclamation 514/2007".

## 2. Amendment

The Diredawa Administration Charter (Amendment) Proclamation No 483/2006 Article 2 is hereby amended as follows:

> "2 The Diredawa provisional Administration term is extended until 7th July, 2007"

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of 5th day of January,2007.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of January, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**